# ለጀነራል አበበ ተክለሀይማኖት፡-እባክዎን ዝም ይበሉ የተንኮሉን ጉድጓድ አያርቁት! –

ሰርጸ ደስታ
May 15, 2017 00:30


ጀነራል አበበ ተክለሀይማኖት

በመጀመሪያ ጀነራል አበበም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው የምሰጠውን አስተያየት በጥሞና ያስተውሉት፡፡ ብዙ ጊዜ እናንተ ትግሬ ወያኔዎች እንደምታስቡት ከጥላቻ ሳይሆን እስካሁን የፈጠራችሁት ችግር ሳያንሳችሁ አሁንም ብልጥ እንሆናለን ባላችሁበት መጠን ኢትዮጵያን አደጋ ላይ እየከተታችኋት መሆኑን ባምንም የሚቀጥሉት አደጋዎች ግን ሲመጡ ዋነኛው የአደጋው ተጋላጮች እናንተው ትግሬ ወያኔዎች እንደሆናችሁ ማሰብን ዛሬም እንዳልቻላችሁ ላስገነዝብ እወዳለሁ፡፡ ጀነራል አበበ ሰሞኑን አገራዊ መግባባት ለብሔራዊ ደህንነት ፖሊሲ ወሳኝ መረጃ ነው በሚል የአስነበቡንን ጽሁፍዎን ለማንበብ ሞክርኩ፡፡ ጽሁፍዎ ከልብዎ የመሰለዎትን ከሆነ በቀጥታ ተሳስተዋልና እባክዎን መረጃው በደንብ ይኑርዎት እላለሁ፡፡ ሆኖም እርሶ የመረጃው እጥረት ኖሮብዎት ተሳሳቱ ለማለት ስለሚከብድ ሆን ብለው ሕዝብን በአላስፈላጊ ውዥንብር ውስጥ ለመክተትና የቡድንዎን(ሕወሐትን) እድሜ ለማቆየት ከዛም ሲያልፍ ደግሞ ከኢትዮጵያውያን የተዘረፈውን የእርሶንና የብዙ ሌሎች እርሶን መሰል የዘመኑ የአገሪቱ ሀብታሞች ንብረት አደጋ ላይ ስለወደቀ ቢያንስ እንደሚሆን ለማዘጋጀት እድል ለመፍጠር ነው፡፡ በዚህ እንስማማ፡፡ ዛሬ ላይ ሁሉም ነገር ገሀድ ወጥቶ ባለበት ሁኔታ መካካዱ አይበጅም፡፡ እንዳልኩት ነው፡፡ ራስዎንም ደግሞ አሁን ከአለው የአገሪቱ ቀውስ ለያግሉ፡፡ እርሶ ለዚህች አገር መፍረስ በመሪነት ከተጫወቱት አንዱ ነዎት፡፡ ከዛሬ 100 በፊት አንድ የሆነችን አገር እየፈረሰች ያለችው ስለ ሕዝብና አገር ምንነት በማይገባችሁ ለአንዷት የግል ነብሳችሁ እጅግ ስግብግብና አረመኔያዊ ባሕሪ በአላችሁ የትግሬ ወያኔዎች ነው፡፡ አሁን መነጋገር የአለብን ቶን በዚህ መልኩ መሆን ስላለበት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እንድትመከሩ ሁላችንም የየራሳችንን ጥረት አድርገናል፡፡ ጭራሽ ስለመከርን እኛንም ለሞትና ለሥቃይ ሴራችሁንም ዛሬ ላይ ራሳችሁን መልሶ በአፈጠጠባችሁ መልኩ ስትጎነጉኑ ኖራችሁ፡፡ አሁንም ከዛው ከተጠናወታችሁ ሴራ መላቀቅና ኧረ ይሄ ነገር አደጋ አለው ትንሽ ቆም ብለን እናስብ ማለት አልቻላችሁም፡፡ ታላቁ መጻፍ እግዚአብሔርን (እውነትን) ለማወቅ በአልፈለጉት መጠን የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ይላል፡፡ በቃ አንዴ ለማይረባ አእምሮ ከተሰጡ ምን ማረግ ይቻላል፡፡ የምትቆፍሩት የተንኮል ጉድጓድ እናንተው የምትወድቁበት ሊሆን እንደሚችል አስባችሁ ጉድጓዱን ቀረብ ማድረግ ብልሀት ነበር፡፡ ይህ በትግሬ ወያኔ ቡድን አይታሰብም፡፡ መስሎን ብዙ ስንመክር ቆይተን ተስፋ ቆረጠናል፡፡

ጀነራል አበባ እስከ አርሶ ያነሷቸውን ጥቂት ነጥቦች ላንሳና እንዴት ከእውነታው ሆን ብለው እንደሚሸሹ ልንገርዎት ሕዝብም ይወቀው፡፡ በመጀመሪያ አሁን ያለው ችግር የተፈጠረው በአለፉት ሁለት ዓመታት ሳይሆን ከዛሬ 26 ዓመት ጀምሮ ነው፡፡ ደርግ ወያኔ ወንበዴ ነው ያለንን አንድ በአንድ ነው በተግባር ያየነው፡፡ ይህ ባሕሪ አይቅፈፍዎት በተግባር ታይቶ ሕዝብ ሁሉ የአወቀው ከዚህ በኋላ በሰፊው የሚሰሙት ስለሚሆን

ሰሞኑን የውጭ ጉዳይና ብሔራዊ ደሕንነት ፖሊሲን ለማሻሻል እንቅስቃሴ ላይ ነው፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ድርድር እየተካሄደ ነው ምናን ይሉናል፡፡ ይሄን እርሶ ነው የሚያዎቁት፡፡ የሆነውም ቢሆን አሁን የሚሰማ የለም፡፡ ለመሆኑ ይህን ጉዳይ ለመጠቆም ለምን ፈለጉ፡፡ ሥራ እየተሰራ ነው ተረጋጉ ነው፡፡ ማንን፡፡ ሕዝቡ እኮ በቃን ብሎ አጋጣሚውን ነው

የሚጠብቀው፡፡ 26 ዓመት አገር ሲያፈርስ የኖረው ብሔራዊ ሳይሆን የወያኔ የሴራ ቡድን ነው እርሶ ብሄራዊ ደህንነት ምናምን የሚሉት፡፡ ለመሆኑ የውጭ ጉዳዩ ማን ነው፡፡ በትግሬ ወያኔ የአገርና ሕዝብ ደህንነትአላዋቂ ግለሰቦች ቡድኑን ነው; በየአገራቱ በአሉ ቆንሲላ ጽ/ቤቶች እንደምናውቀው ወይ ዋናው ከአልሆንም ምክትሉ ትግሬ ወያኔ ከአልሆነ አገሪቱ ውክልና የላትም፡፡ ከሥር ያሉት ,ሠራተኞችን ሳናስብ ማለት ነው፡፡ ሊሻሻል የታሰበው እንዴት ነው; ትግሬ ወያኔ እንደሆነ እንኳን ለኢትዮጵያ ማሰብ ይቅርና ለራሱ እኳን ለመጠንቀቅ ስግብግብነት የአወረው ቡድን ነው፡፡ አሰብን ከኢትዮጵያ በግድ ነጥቃችሁ ለሻቢያ ስትሰጡ ጀምሮ አሳምረን እናውቃችኋለን፡፡ ሌላው ከደህንነት ጋር የተገኛኘውን የታጠቀውን አካል እንመልከት፡፡ የትግሬ ወያኔ ቡድን ሙሉ በሙሉ የሚመራው አደለም; በከተማና በመንደር ሰላማዊ ዜጎችን የሚገድል የታጠቀ ቡድን፡፡ የደርግ ሰራዊት በብዙ መልኩ ኢትዮጵያዊነት ነበረው፡፡ መሪዎቹም ዘር ጎሳ ሳይሆን ችሎታን መሠረት የአደረገ ነበር፡፡

በስነምግባር ቢነቀፍም፡፡ ዛሬ የአለው ሊያውም በዚህ ዘመን የአለም አስተሳሰብ ፍጹም ከደርጉ በተለየበት ዘመን የዳር ድንበር ጠባቂ ሳይሆን በከተማ ዜጎችን የሚፈጅ ሰራዊት ነው በኢትዮጵያ መከላከያ ሥም የሚጠራው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ በኋላ ቀን እየቆጠረለት እንጂ ዋነኛ ጠላቱ የወያኔ ሰራዊት እንደሆነ እርሶም አጥተውት አደለም፡፡ ተራው ወታደር ማለቴ አደለም ሰራዊቱን የወከሉት ባለሥልጣናት እንጂ፡፡ ተራው ወታደር የሕዝብን አጋጣሚ እስከሚያገኝ ነው፡፡

ወደሕዝቡ እንደሚቀላቀል ግልጽ ነው፡፡ እርሶም እኮ እዛ ነበሩ፡፡ በግልዎ ማን እንደነበሩ እራስዎ ይወቁት፡፡ እኛ ይሄ ነገር አይሆንም በዲፕሎማሲውም በሰራዊቱም በችሎታ እንጂ በትግሬነት አይሁን ስንል ጭራሽ ጥቂት አንድ አንድ የነበሩትን የሰራዊቱ አመራርም አስወጥታችሁ ሙሉ በሙሉ በትግሬ ተካችሁ፡፡ በተለይ ከ 97 ቱ ምርጫ በኋላ ሰበብ እየፈለጋችሁ ሌሎችን ማስወጣት ብቻም ሳይሆን ወደ መግደልና ማሰርን ዋነኛ ዘዴ አደረጋችሁ፡፡ ሌሎችንም ወሳኝ ተቋማት እንይ ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድና የጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያቤት፡፡ የስግብግብነታችሁ መጠን እኮ አውሮአችሁ እናንትን የሚታወቃችሁም ለመሆኑ እጠራጠራለሁ፡፡ የአገርና ሕዝብ ደህንነት እየፈረሰ ያለው እንዲህ በአለ ውንብድና ነው፡፡ ኢላማ መደረግ ከአለበት ይሄው ነው፡፡ የእርሱ ከመሠረታዊ እውነታው የወጣ ዙሪያ ጥምጥም ማደናገሪያ የሚያዋጣ አይመስለኝም፡፡ ይሄ እኮ ታች ያለው ገበሬ ሳይቅር የሚያውቀው ገሀድ ነው፡፡

ሌላው ስለሕዝብ እልቂት ብዙም ሳይሉ ስለንብረት መውደም ሊያሳስቡን ሞክረዋል፡፡ አይምሰልዎት ስለማን ንብረት ነው የሚያወሩት; አሁንም የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህ ይለዩት፡፡ በ 26 ዓመት ከምንም ተነስተው የአገርን ንብረት ዘርፈው ሚሊየነር የሆኑት የኢትዮጵያ ሕዝብ ገዳይ ጠላቶች ትግሬ ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አደለም፡፡ እና ይሄን ንብረትና እርሶ ኢንቨስትመንት ያሉት ሕዝብን ከቦታው እያፈናቀለና ሜዳ እየጣለ ያለውን የወያኔ ትግሬዎችና ደጋፊዎቻቸውን ኢነቨስትመንት ነው የሚሉት፡፡ እስከዛሬም የሕዝቡን ጨዋነት ልታደንቁ በተገባችሁ፡፡ ግን አእምሮአችሁ በትዕቢትና በስግብግብነት ስለታወረ ማሰብ አትችሉም፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብን እየጨረሰ ያለው የእናነተ ንብረት ነው፡፡ ቀጥሎ ግን ስለንብረት ሳይሆ ነብሳችሁን የምታስጠልሉበትን ቦታ የት ባገኝት የምትሉበት ወቅት እንዳይመጣ እሰጋለሁ፡፡ አያያዛችሁ ወደዛው የሚያመራ ነውና፡፡ የሚያሳዝን ነው አንድም ውስጣችሁ ረጋ ብሎ ማሰብ የቻለ የለም፡፡ ላስታውስዎት እርሶ ዛሬ ከሲስተሙ ውጪ ነኝ እንደሚሉት ሳይሆን አሁንም የሥርዓቱ አገልገይ ሆነው በውጭ አርበኝነት እንደተሰማሩ አስተያየትዎ ስለሚያሳብቅ ነው፡፡ ልብ ይበሉ ቀጥሎ ንብረትን ሳይሆን ንብሳችንን የት እናኑራት የምትሉበት ያኩት ለማስፈራራት አይምሰልዎት፡፡ ብዙ ጊዜ ሲነገራችሁ የማትሰሙ እንደሆነ ባውቅም ይህ ሲሆንም እንዲታስታውሱት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች እንደትንቢት ሲነግሯችሁ ነበር፡፡ አልሰማችሁም፡፡ እውነታው ለሰዎች ግልጥ ብሎ የሚታይ ነው ነብይነት የሚያስፈልገው አልነበረም፡፡ እናንተን ግን ስግብግብነት ስለአወራችሁ ጭራሽ ሌላ ሴራ እያሴረችሁ ዛሬ ለመወጣት አዳጋች ወደሆነ ጉድጓድ ሁኔታዎችን መራችኋቸው፡፡

ሌላው በሕዝቦች ዘንድ የተፈጠረውን አለመግባባት ሊያነሱ ይሞክራሉ፡፡ እና ሕዝብን በፖሊሲና ስተራቴጂ የመከፋፈል አጀንዳ ይዞ ለ 26 ዓመት ሲሰራ የነበረውን ወያኔን እንዴት ጥፋቱን እንኳን ለመጠቆም ዘነጉት፡፡ እባክዎን አሁንም ሌላ ችግር ከመፍጠር ወይ ዝም ይበሉ መፍትሄ ከአሉ ደግሞ በብዙ ሳይሆን ጥቂት እውነትም እየጨመሩበት ይሁን፡፡ ሙሉ ለሙሉ አይቻልዎትም፡፡ እግረመንገድዎንም እውነትን ይለማመዳሉ፡፡ እስኪ እኔ ድጋሜ ከምለፋ ይችን ሊንክ ይመልከቱ

https://www.youtube.com/watch?v=sz3M9jiwxow . ብዙ እንዲህ ያሉ ምክሮች ተሰጥተው ነበር፡፡ ምንአልባት እንዲህ ያለ ነገር የተናገሩ ዛሬ በሕይወት የሉም፡፡ የሕዝቦች መከፋፈሉን እንዴት እንዳመጣችሁት እናነተም አልጠፋችሁም፡፡ ችግሩ በስግብግብነት ስለታወራችሁ በራሳችሁ ላይ ተመልሶ ሊመጣ እንደሚችል እኳን አልቻላችሁም፡፡

ሌላው ስለሕገመንግስት ምናምን አንደማንኛውም ወያኔና ደጋፊው አግዝፈው ያወራሉ፡፡ ሰዎ እኮ ስልችት ነው ያለው፡፡ ሲጀምር ሕገመንግስት የሚሉት ከጅምሩም የወያኔ ትግሬዎችን ሕይወት ለማራዘም ታስቦ የተዘጋጀ እንጂ የኢትዮያን ሕዝቦች መሠረት ያደረግ አደለም፡፡ ከእነ ችግሩ ሆኖም ሕዝብ ቀሪ የተጻፈለችለትን ሙብት ሲጠይቀ ወይ አሸባሪ ነው ወይም ሌላ ሥም ይሰጠውና ወይ ሞት ወይ የማሰቃያ ማጎሪያዎች ነው የሚከማቸው፡፡ በዚህ ሕገመንግስት ዝግጅት ተሳታፊ የሆናችሁት ሁለቱ የአገርና የሕዝብ ጠነላቶች ወያኔና ኦነግ እንደሆናችሁ ሕዝቡ ያውቃል፡፡ ዲሞክራሲንም ሊያሱት ያስባሉ፡፡ ምን አልባትም ስልጣን እንደያዛችሁ ስለምትፈሩም ነው መሠለኝ የተሻለ ሁኔታ ነበር፡፡ ውስጥ በውስጥ ሴራችሁን ብትቆፍሩም እንደዛሬው ገኖ አልወጣም፡፡ ፍፁም የወንብድና ተግባር በሕዝብና አገር ላይ በመዋቅር እየተፈጸመ ስለዲሞክራሲ ቃሉን እንኳን መናገር እንዴት ሞራል እንዳገኙ አይገባኝም፡፡ ለነገሩ ሌላው የወያኔ ትግሬዎች ባሕሪ እፍረተ ቢሲ መሆን ነው፡፡ በ 10 ሺዎች በጠራራ ጸሀይ በመንገድ በሚገደሉባት አገር፣ በ 100 ሺዎች በእስር ታጉረው በሚሰቃዩባት አገር ዲሞክራሲ ሲሉ በሕዝብ እንደማላገጥ ስለሚታሰብ ጭራሽ ሕዝብን ማነሳሳት እንዳይሆንብዎት፡፡ አሁንም አልላለሁ እባክዎን ዝም ይበሉ፡፡ አይችሉበትም

የተቃዋሚዎችንም ድርድር አንስተዋል ለካ፡፡ አነማን ናቸው; ዛሬ ሁሉም ኢትዮጵያ እንደ ብቸኛ ሰላማዊና እውነተኛ ተቃዋሚ የሚቆጥራቸው እነ ዶ/ር መረራና አባላቶቹ የት ነው ያት፡፡ መረራ ብዙ ጊዜ ሲናገሩት የነበረው ነገርም እኮ ትንቢት አልነበረም፡፡ ኧረ ተው አብዮት ልጁን ትበላለች፡፡ ይህ ነገር ሕዝቡ በኋላ መሪውን ይበላል ሲላችሁ ነበር፡፡ አንዴ አደለም፡፡ በተደጋጋሚ፡፡ መረራን እስከዛሬ ብዙም የኦሮሞ ሕዝብ አይደግፈውም ብላችሁ ስለምታምኑ ስጋት አልሆነባችሁም ነበር፡፡ ዛሬ ግን አደለም ብዙ ኦሮሞዎችና ሌሎች አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ፍልስፍናውን አንደተከተሉ ስታዩ አሸባሪ አደረጋችሁት፡፡ በቀለን ጎነደሮች በመዲናቸው ሥሙን ከፍ ያደረጉበት ምክነያት ይገባችኋል፡፡ በስግብግብነት ስለታወራችሁ ምን ያህል ሕዝቡ ጥሏችሁ እንደሄደ እናንተ አይገባችሁም፡፡ የወያኔው ጌታቸው በይፋ ኦሮሞና አማራ እንዴት አንድ ይሆናል ሲል የበረቀበት ምን ያህል ባዶ እንደሆናችሁ ሕዝብ አውቋችኋል፡፡ የቀራችሁ የኖራችሁበት ስግብግብነትና አረመነያዊ ጭካኔ ነው፡፡

ልብ ይበሉ በግፍ በየእስርቤት እየተሰቃዩ ስላሉት ዜጎች፣ ጋዜጠኞችና የፖለቲካ አመራሮችን ጨምሮ ከእስር ስለመፈታት የመፍትሄ አካል አንዱ አንደሆነ መናገር አልፈለጉም፣ በትግሬ ወያኔ እጅ ሙሉ በሚሉ የተያዙ ተቋማት በሌሎች ችሎታዎ ባላቸው መተካትን መፍትሄ አካል አልታዎትም፣ ሕገ መንግስት ምናምን የሚለው ቀርቶ ሕዝብን የሚያግባባ የጋራ ስጋት የሌለው መወያያን አይናገሩም፡፡ ሁሉንም እርሶና ቡድንዎ የሚድኑበትን የመሰለዎትን ብቻ ሲዘረዝሩ እስከታች ይዘልቃሉ፡፡ እሱም የቃላት አጀብ እንጂ ይህ ነው የሚባል ውል ያው መልዕክት እንኳን ማንበብ አይቻልም፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሸባሪ ተብሎ ክተት ታውጆበታል፡፡ ከዚህ በኋላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከእስከዛሬው የከፋ ነገር አይመጣበትም፡፡ ቢመጣም ከኢትየጵያ ሕዝብ በፊት ተጠቂው ሕዝብን አሸባሪ የሚለው በእርግጥም ራሱ የአሸባሪነት ሁሉ ባሕሪዎች ያሉት የትግሬ ወያኔና ደጋፊዎቹ ቡድን ነው፡፡ እርግጥ ነው መጨረሻው ለኢትዮጵያም መበታተን አደጋ አለው፡፡ ከዛ በፊት ግን የትግሬ ወያኔና ደጋፊዎቻቸው ይጠፋሉ፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ለ 26 ዓመት እንዲጠፋ ብትዘምቱበትም አሁንም እንደታመቀ ነው፡፡ የመዳን እድሉም ሰፊ ነው፡፡ እናንተ ግን እየቀረላችሁ አይመስልም፡፡ ጥቂቶች ቀድመው ወደ ተዘጋጁበት አገር ሊሰደዱ ይችላሉ፡፡ ብዙዎቹ ግን ስግብግብነትና ከፋት አውሯቸዋልና የሚቀርላቸው አይመስለኝም፡፡ አሁንም እድሉ ነበራቸው፡፡ ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ነው፡፡ በማይረባ አእምሮ ስለተለከፉ እየቆፈሩ ያሉትን ጉድጓድ መደፈኛ ከመሆን እያመለጡ አይመስልም፡፡ እርሶም መፍትሄዎቹን በግልጽና በአጭር ሁኔታ መግለጽ ሲችሉ የሴራውን ጉድጓድ በማራቅ ተሰማረተዋል፡፡ አዝናለሁ፡፡ ይህ መልካም ጥቆማ ነው፡፡ ከዚህ በፊትም እንዲሁ ያለ ሴራ ሲያሴሩ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ጀንራል ጻድቃንም እንዲሁ፡፡ አይገባችሁም ልበል; ከዚህ ቀጥሎ በየትኛውም ሰዓት ሊሆን እንደሚችል ይወቁ፡፡ በተረፈ ዝም ቢሉ ቢያንስ ለግልዎ መልካም ነው፡፡ ለሄላው አላስፈላጊ በሆነ መልኩ የኢንግሊዘኛ ቃላትን በመጠቀም ሊያብራሩ የሚሞክሩት በፍልስፍና ስህተት ነው፡፡ ነገሮችን መዛባት መሞከረ ነው፡፡ አማርኛዎቹ የበለጠ ጋላጭ ናቸው አብዛኞቾ፡፡ የዕውቀትም መገለጫ አደለም፡፡ በተረፈ እንደወረደ ለተጠቀምኳቸው ቀላቶች እውነት ስለሆኑ እንጂ ለመሳደብ ወይም ለመኮነን

አደለም፡፡ እንዲም መነጋገር የግድ ስለሚል ነው፡፡ ከዚህ ውጭ መፍትሄ የሚሆኑ ሺ አሳቦች አሉ ግን በአሁን ወቅት ብቸኛ መፍትሄ እንዲሆን እያደረጋችሁ ያላችሁት የኖራችሁበትን ሴራችሁን ነው፡፡ አዝናለሁ!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይጠብቅ!

አሜን!
ሰርጸ ደስታ